COLORADO
Office of Economic Development & International Trade

# የኮሎራዶ የጅማሪ ብድር ፈንድ/ Colorado Startup Loan Fund

ጠቅላላ መረጃ
አይነት: ብድሮች
ለ: አነስተኛ የንግድ ድርጅቶች የሚሰጡ
የገንዘብ መጠን: $31.35 ሚሊዮን ይቀርባል
የማመልከቻ ጊዜ: ማመልከቻዎች በ2021 ዓ.ም መጨረሻ ላይ ይከፈታሉ
የ**OEDIT** ምድብ: የንግድ ስራ የገንዘብ ድጋፍና ማበረታቻዎች

የኮሎራዶ የጅማሪ ብድር ፈንድ/ Colorado Startup Loan Fund የስራ መጀመሪያ፣ መልሶ መጀመሪያ ካፒታል ወይም የንግድ ስራቸውን መልሰው ማዋቀር ለሚያስፈልጋቸው እና ከባህላዊ አበዳሪዎች ብድር ማግኘት ለማይችሉ የኮሎራዶ የፈጠራ ባለቤቶችና የአነስተኛ ንግድ ድርጅት ባለቤቶች ብድሮችና አነስተኛ እርዳታዎች ይሰጣል። ይህ ተዘዋዋሪ ፈንድ ማለትም ዶላሩ ብድሩ ተመልሶ በሚከፈልበት ወቅት አዳዲስ የፈጠራ ባለቤቶችን በመደገፍ ለመቀጠል ጥቅም ላይ የሚውል ነው።

ምንም እንኳን የCOVID-19 ወረርሽኝ በተከሰተበት ወቅት ሁሉ አሁን ያሉ የንግድ ድርጅቶችን በፋይናንስ ሀብቶች ለመደገፍ ከፍተኛ ጥረቶች የተደረጉ ቢሆንም ብዙ የንግድ ስራ ድርጅቶች ተዘግተዋል። በዚህም የተነሳ የመመለስና አዲስ ፍላጎትን ለማሟላት አዳዲስ የንግድ ድርጅቶችን መክፈት የሚቻልባቸው እድሎች አሉ። በCOVID-19 ምክንያት ኪሳራ እንዳጋጠማቸው ወይም ድርጅታቸውን እንደዘጉ ያስመዘገቡ የፈጠራ ባለቤቶች በዝቅተኛ የብድር ክፍያ ውጤቶች ወይም በሌሎች ከወረርሽኙ ጋር ተያያዥ የፋይናንስ ተጽእኖዎች የተነሳ መልሰው ወደ ገበያው እንዳይገቡ ሊገደቡ ይችላሉ። ይህ ፈንድ በወቅቱ ገበያ ውስጥ ለመስራት ለሚደረግ አዲስ የንግድ ስራ ፈጠራ እና አሁን ያሉ ድርጅቶችን መልሶ ለማዋቀር ድጋፍ ያደርጋል።

ብቁነትና የማመልከቻ ሂደትን ጨምሮ የፕሮግራሙ ዝርዝሮች በግልጽ ተቀምጠዋል። ማመልከቻዎች በ2021 ዓ.ም ማብቂያ ላይ ይከፈታሉ። የፕሮግራሙን ወቅታዊ መረጃዎች ለማግኘት በOEDIT ኢሜይል ይመዝገቡ።

ፈንዱ በሚከተሉት ላይ ትኩረት ያደርጋል:

- አሁን ያሉ የንግድ ስራ ሞዴላቸውን መልሰው ለማዋቀር፣ ለማደራጀት ወይም በCOVID-19 ወረርሽኝ ምክንያት መልሰው በካፒታል ለመደገፍ የሚፈልጉ የንግድ ስራ ድርጅቶች
- በCOVID-19 ወረርሽኝ መከሰት ባጋጠሙ መዘጋቶች ምክንያት በማህበረሰቡ ወይም ኢንዱስትሪው ላይ የተፈጠሩትን ክፍተቶች የሚያስመዘግቡ አዳዲስ የንግድ ድርጅቶች
- በCOVID-19 ወረርሽኝ መከሰት ምክንያት በባህላዊ ምንጮች አማካኝነት ካፒታል የማግኘት አቅማቸውን የሚገድቡ የፋይናንስ ኪሳራዎች ወይም ሌሎች ተጽእኖዎች ያጋጠሟቸው የፈጠራ ባለቤቶች
- ከባህላዊ ምንጮች ካፒታል ለማግኘት እንቅፋቶች ያጋጠሟቸው ሰዎች

ፕሮግራሙን ለማስተዳደር ከተልዕኮ ተኮር ለትርፍ የማይሰሩ አበዳሪዎችና የማህበረሰብ ልማት የፋይናንስ ተቋማት (CDFIs) ጋር በትብብር እንሰራለን። ከእነዚህ ድርጅቶች ጋር መስራት የሚያስገኘው ጥቅም:

- መደበኛ የባንክ ግምቶችና የብድሩ መጠን ባህላዊ አበዳሪዎችን ብድር ከመስጠት በሚገድብበት ሁኔታ ብድር መስጠት
- የበለጠ ተለዋዋጭ የመልሶ ክፍያና መልሶ ማዋቀር አማራጮች ይፈጥራል
- ተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ ያደርጋል እንዲሁም ከባህላዊ አበዳሪዎች ይልቅ የማህበረሰቡን ሁኔታ ለመረዳት በጥልቀት ለመድረስ ያስችላል
- ተልዕኮ ተኮር በመሆኑ ምክንያት የማበደሪያ ተመኖችና ክፍያዎች በክሬዲት ካርዶች ወይም የፔይሮል አበዳሪዎች ከሚቀርቡት አንጻር ዝቅተኛ ናቸው
- ተጨማሪ የባህላዊ የካፒታል ምንጮችን ለመድረስ ላልቻሉ ህብረተሰቦችና የንግድ ድርጅቶች የኢኮኖሚ መሻሻል ድጋፍ ያደርጋል

ለፕሮግራሙ ዝግጅት የሚያገለግል ግብአት ይሰጣል